በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም - ክፍል 3

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ነሐሴ ፳ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የእመቤታችን ሕይወት

***እረፍቷ***

- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በኢየሩሳሌም አቅራቢያ በምትገኘው በደብረ ዘይት ስትጸልይ ሳለ ቅዱስ ገብርኤል በመጀመሪያ በናዝሬት እንዳነጋገራት ሁሉ ከገነት የተገኘ ነጭ ቀለም ያለው አበባ ይዞ በመገለጥ "የምድር ዘመንሽ በቅርቡ ተፈጽሞ ልጅሽ አምላካችን ወደ ራሱ ይወስድሻል።" በማለት ነገራት።
- ጊዜውም ሲደርስ ልጅዋ ጌታችን አምላካችን ሐዋርያት ከየሚያስተምሩበት አህጉር በኢየሩሳሌም እንዲሰባሰቡ አደረገ።
- በጊዜውም እመቤታችን ስታርፍ እመቤታችን የነረችበት ቤት በታላቅ ብርሃን ተሞላ።
- ጌታችንም በመላእክቱና በቅዱሳኑ ተከቦ ንጽሕት ነፍስዋን ወሰደ።
- ስትመኝ ነበርና ሐዋርያትም ሥጋዋን አባትና እናትዋ በተቀበሩበት በደብረ ዘይት ተራራ ግርጌ በምትገኘው በጌቴሴማኒ ቀበሩዋት።
- በምትቀበርበትም ጊዜ ብዙ ተአምራት ተደርገዋል።
- የእግዚአብሔር እናት እመቤታችንን በድን የሚገኝነትን ሽንኮር በመንካት እውራን ብርሃን አዩ፣ አጋንንት ከሰዎች ወጡ፣ ብዙ ደዌያት ያሉባቸውም ሕሙማን ተፈውሱ።
- የእመቤታችንን ከቀበሩ ከሦስት ቀናት በኋላ ሐዋርያው ቶማስ ደረሰ። ከማረፍዋ በፊት ሊያያትና ክብርንም ሊሰጣት ተመኝቶ ስለነበር እጅግ አዘነ።
- በዚህም የተነሳ እመቤታችን የተቀበረችበትን መቃብር ሲከፍቱት ከተገነዘችበት ልብስ በቀር በድኗ ግን አልተገኘም። አሁን ለምንጾመው የፍልሰታ ጾም መሠረቱ ይኸው የቶማስ ነገር ነው።
- ሐዋርያትም ተደንቀው ወደ ቤታቸው ተመልሰው በጸሎት ሰዓታቸው ሲጸልዩ ሳሉ የመላእክትን ዝማሬ ሰሙ።
- ፈጥነውም ወደ ላይ ቢመለከቱ እመቤታችንን በታላቅ ሰማያዊ ክብር በመላእክት ተከባ አዩአት። ደቀ መዛሙርቱንም "ቀንም ሆነ ሌት ከእናንተ ጋር ነኝና ደስ ይበላችሁ!" አለቻቸው።

# የእመቤታችን ሕይወት

- እመቤታችን ሰማያዊት እናት በመሆን እስከዛሬ ድረስ ይኽንኑ ቃልኪዳንዋን እየፈጸመችልን ነው፡፡
- ስለ ጥልቅ ፍቅርዋና ብርታት ስላለበት ረዳትነትዋ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ክብርን እየሰጠን ትረዳን ዘንድ የነቢዩ ኢሳይያስን፣ የቅድስት ኤልሳቤጥን ፈለግ በመከተል ስለእመቤታችን በኤፌሶን ጉባኤም (431 ዓ.ም.) ከሐድያንን በመርታት ተረጋግጦ በተወሰነልን መሠረት የእግዚአብሔር ወይም የአምላክ እናት ናት ከማለት ጋር "ለክርስቲያን ወገኖች ሁሉ የምታማልጂ መልካሚቱ ርግብ፣ ያዘኑ ሁሉ መጽናኛና ደስታቸው እመቤታችን ሆይ እረፍትሽም ባልገታው አማላጅነትሽ አማልጅን - ጸልይልን፡፡" እንላታለን፡፡
- እመቤት ብሎ መጥራትም በቅዱስ መጽሐፍ ያለ ትምህርት ነው፡፡ <u>*ካል ዮሐ 1፡2-5፡፡*</u>
- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ፍጹምነትን ለሚሹ ሁሉ አስተማሪ የሆነች የመጀመሪያይቱ እናት ናት፡፡ መላ ሕይወትዋን ለእግዚአብሔር በመስጠት ለእግዚአብሔር ቤትስ አገልግሎት ከሆነ በድንግልና መኖር በጋብቻ ከመኖር የላቀ እንደሆነ አስተምራለች፡፡
- ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን አንስቶ የሰው ወገኖች ልጅዋን አምላካችን መድኃኔዓለምን፣ እርስዋን፣ ነቢያቱንና ሐዋርያቱን ምሳሌ በማድረግ ሕይወታቸውን በድንግልና፣ በጸሎት፣ በጾም፣ በጽሙና፣ በብህትውና፣ መምራት ጀምረዋል፡፡
- የምንኩስና ሕይወት የመነጨውም በአንድ በኩል ከዚሁ ነው፡፡ ይህን ተከትሎም በርካታ ገዳማት በቅድስና ሕይወት ለመኖርና መንፈሳዊ ጥበባትንም ለመቅሰም የሚቻልባቸው ምንጮች ሆነዋል፡፡
- ዛሬ የእግዚአብሔር ፈቃድ በማይደረግበት ዓለም እንዲህ ያለው የድንግልናና የንጽሕና ሕይወት የማይደነቅ አንዳንድ ጊዜም "በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፥ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፥ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ፡፡ <u>*ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው*</u>፡፡" ያለውን አምላካዊ ቃል በመዘንጋት ትኩረት የማይሰጠው እየሆነ ይገኛል፡፡
- እመቤታችን የአምላክ እናት እንድትሆን ከተመረጠችበት አንስቶ ቀጥሎም አረጋዊው ስምዖን "ስምዖንም ባረካቸው እናቱን ማርያምንም፡፡ እነሆ፥ የብዙዎች ልብ አሳብ ይገለጥ ዘንድ፥ ይህ በእስራኤል ላሉት ለብዙዎቹ ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሞአል፥ <u>*በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል*</u> አላት፡፡" <u>*ሉቃ 34-35፡፡*</u> እንዳላት በልጅዋ ፊት በመጽናት ስላሳየችው ሕይወት ልጅዋ ጠላት ዲያቢሎስን ድል ካደረገ በኂላ የምንገኝ እኛ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ሁሉ ከፍ ከፍ እናደርጋታለን፡፡

# የእመቤታችን ዘላለማዊ ድንግልና

***ለእግዚአብሔር መለየትዋ***

- የአይሁድ ባሕል ድንግልናንና መታቀብን ደስ የሚያሰኝን ነገር ከመተው ጋር ሳይሆን የእግዚአብሔር መንፈስ ለወገኖቻቸው ድኅነት መፈጸም ሲል ሕይወቱ በእግዚአብሔር በተቀደሰለት ወይም በተመረጠለት ሰው የሚፈጸም አምላካዊ ሥራ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡
- እመቤታችንም ድል አድራጊ ለሆነው አምላካችን ማረፊያው መሳሪያው ሆና ተመርጣለች፤ ሰማይና ምድር የማይችሉትንም በሥጋ ወልዳዋለች፡፡ *ዘፍጥ 3፡15፣ ማቴ 1፡20-21* እንደተጠቀሰው ከዘርዋ - ከሥጋዋ በመንፈስቅዱስ የተወለደው እርሱ የጠላትን ራስ በመስቀሉ ኃይል ቀጥቅቶታል፡፡
- ይህ ነፍስና ሥጋዋ ለእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ብቻ ማቅረብዋን ንጉሡም የሥጋዋንም የነፍስዋንም ንጽሕና የወደደ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ «በእግዚአብሔር ፊት ባለሟልነትን አግኝተሻልና…» *ሉቃ 1፡30፡፡*
- እነዚህንም ነጥቦች ነቢዩ ሕዝቅኤል እንደ ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢት መነጽር ተመልክቶ “ወደ ምሥራቅም ወደሚመለከተው በስተ ውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ ተዘግቶም ነበር፡፡ እግዚአብሔርም፦ ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፥ ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል፡፡” *ሕዝ 44፡1-2* በማለት ጌታ እግዚአብሔር በታተመው መቅደስ ውስጥ ከመግባቱ ጋር በማነጻጸር እንመልከት፡፡
- አረጋዊው ዮሴፍም የእጮኛው የእመቤታችን ከመንፈስቅዱስ የሆነ መጽነስና በመንፈስቅዱስም መውለድ እንዲሁም የአምላክ ሥጋ መልበስና የእመቤታችን ነገር እርሱ ከለመደውና ከሚያውቀው የተለየ ሊሆንበት እንደሚችል መረዳትም አያስቸግርም፡፡
- የኪዳኑን ታቦት መንካት ያዛን “ወደ ናኮንም አውድማ በደረሱ ጊዜ በሬዎቹ ይፋንኑ ነበርና ያዛ እጁን ዘርግቶ የእግዚአብሔርን ታቦት ያዘ፡፡ የእግዚአብሔርም ቍጣ በያዛ ላይ ነደደ፥ እግዚአብሔርም ስለ ድፍረቱ በዚያው ቀሠፈው በእግዚአብሔርም ታቦት አጠገብ በዚያው ሞተ፡፡” *ካል ሳሙ 6፡6-7* እንደተባለው ሕይወት ካስከፈለው ሕግጋትን፣ መዝሙራትን፣ ትንቢታትን የሚናገሩ የመጻሕፍት ጥቅሎች የእግዚአብሔር ሰው የሆነው አረጋዊው ዮሴፍ የሥጋ ፈቃዱን መፈጸሙን አስመልክቶ ካልነገሩን ለእሥራኤል ዘነፍስ መዳን ዙፋኑ እንድትሆነው የመረጣትን እመቤታችንን ከመጠበቅ የዘለለ ሌላ ያደርጋል ወይም አድርጓል ብለን ስለምን እናስባለን?

# የእመቤታችን ዘላለማዊ ድንግልና

***የጌታ ‹‹ወንድሞች››***

- በቅዱስ መጽሐፋችን ጌታችን "ወንድሞች" እንዳለው የሚናገሩ ዘጠኝ ጥቅሶች ይገኛሉ፡፡ ማቴ 12፡46-47፣ ማቴ 13፡55-56፣ ማር 3፡31-32፣ ማር 6፡3፣ ሉቃ 8፡19-20፣ ዮሐ 2፡12፣ ዮሐ 7፡3-5፣ የሐ ሥራ 1፡14፣ እና ቀዳ ቆሮ 9፡5፡፡
- በነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የያዙት "ወንድም" የሚለው ቃል በግሪኩ *adelphos* ተብሎ ይታወቃል፡፡
- ሐዋርያት የተጠቀሙበት፣ በሰባው ሊቃናት ከዕብራይስጥ (እስራኤል) ወደ ጽርዕ (ግሪክ) ቋንቋ በተረጎሙት ጥንታዊው የግሪኮች ብሉይ ኪዳን - The Septuagint ዘመድ የሚለውንም ቃል *adelphinos* እና *anepsios* በሚል ቃል ተጠቅሞበት እናገኘዋለን፡፡
- *adelphos* የሚለው የግሪኩ ቃል «ወንድም»፣ «ዘመድ»፣ «አምኖ የተከተለ»፣ «የአንድ አገር ሰው»፣ «የወንድ የቅርብ ዘመድ» የሚሉ ትርጉሞችን በመያዝ በግሪኩ The Septuagint ውስጥ ይገኛል፡፡
- ***ዘፍጥ 14፡14-16፣ ዘፍጥ 29፡12፣ ዘሌዋ 25፡49፣ ኤር 32፡8፣ ኤር 32፡9፣ ኤር 32፡12፣ ጦቢት 7፡2*** ወዘተ ወንድም የሚለው ቃል የተለያዩ ወገኖችን የሚመለከት እንደሆነ ያረጋግጡልናል፡፡
- ለምሳሌ ሎጥ « የታራም ትውልድ እነሆ ይህ ነው፡፡ ታራ አብራምንና ናኮርን ሐራንንም ወለደ ሐራንም ሎጥን ወለደ፡፡ ሐራንም በተወለደበት አገር በከለዳውያን ዑር በአባቱ በታራ ፊት ሞተ፡፡ አብራምና ናኮርም ሚስቶችን አገቡ የአብራም ሚስት ስምዋ ሦራ ነው የናኮር ሚስት የሐራን ልጅ ሚልካ ናት ሐራንም የሚልካና የዮስካ አባት ነው፡፡ ሦራም መካን ነበረች ልጅ አልነበራትም፡፡ ታራም ልጁን አብራምንና የልጅ ልጁን የሐራንን ልጅ ሎጥን የልጁንም የአብራምን ሚስት ምራቱን ሦራን ወሰደ ከእርሱም ጋር ወደ ከነዓን ምድር ይሄዱ ዘንድ ከከለዳውያን ዑር ወጡ ወደ ካራንም መጡ፥ ከዚያም ተቀመጡ፡፡» ***ዘፍጥ 11፡27-31፡፡*** እንደተባለው የአብርሃም የወንድሙ ልጅ ነበር፡፡

# የእመቤታችን ዘላለማዊ ድንግልና

***የጌታ ‹‹ወንድሞች››***

- *ነገር ግን* « *አብራምም ሎጥን አለው፦ እኛ ወንድማማች ነንና በእኔና በአንተ በእረኞቼና በእረኞችህ መካከል ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለሁ*።» ***ዘፍጥ 13፡8***፣ « *በሰዶም ይኖር የነበረውን የአብራምን የወንድም ልጅ ሎጥን ደግሞ ከብቱንም ወስደው ሄዱ*።… *አብራምም ወንድሙ እንደ ተማረከ በሰማ ጊዜ በቤቱ የተወለዱትን ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ብላቴኖቹን አሰለፈ፥ ፍለጋቸውንም ተከትሎ እስከ ዳን ድረስ ሄደ። ብላቴኖቹንም ከፍሎ በሌሊት እርሱ ከባሪያዎቹ ጋር ወረደባቸው፥ መታቸውም፥ በደማስቆ ግራ እስካለችውም እስከ ሖባ ድረስ አሳደዳቸው። ከብቱንም ሁሉ አስመለሰ፥ ደግሞም ወንድሙን ሎጥንና ከብቶቹን ሴቶችንና ሕዝቡን ደግሞ መለሰ*። » ***ዘፍጥ 14፡14-16*** *በማለት ሎጥ እንደ ወንድም ተጠቅሶ እናገኛለን*።
- *በቅዱስ መጽሐፋችን ውወጥ በየትኛውም ክፍል እመቤታችን የጌታ «ወንድሞች» እናት እንደሆነች ተለይቶ ተጠቅሶ አልተጻፈልንም*።
- *እመቤታችን ሌሎች ልጆች ቢኖሩአትስ ጌታ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ተሰቅሎ ሳለ እናቱን በአደራ ለወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ይሰጠው ነበርን?*

***‹‹እስከ›› የሚለው ቃል ትርጉም***

- *ስለ እመቤታችን ዘላለማዊ ድንግልና ሲነሳ የሚነሳው ሌላው ጥያቄ ማቴ* 1፡25 *«የበኲር ልጅዋንም **እስክ**ትወልድ ድረስ አላወቃትም*፤ *ስሙንም ኢየሱስ አለው*።» *በሚለው ጥቅስ ውስጥ የሚገኘው «እስከ» ነው። ከወለደች በኂላ አወቃት ለማለት ይጠቀሙበታል*።
- *በቅዱስ መጽሐፍ «እስከ» የሚለው ቃል የተለያዩ ትርጉሞች ያሉት መሆኑን በሚከተሉት ጥቅሶች መረዳት ይቻላል*።
- *«የሳኦልም ልጅ ሜልኮል **እስከ** ሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አልወለደችም*።» ***ካል ሳሙ 6፡23***፣ *«በዘመኑም ጽድቅ ያብባል፥ ጨረቃም **እስኪ**ያልፍ ድረስ ሰላም ብዙ ነው*።» ***መዝ 71፡7***፣ *«እግዚአብሔር ጌታዬን፦ ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ **እስካ**ደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው*።» ***መዝ 109፡1***፣ *«አንቺም ቅፍርናሆም፥ **እስከ** ሰማይ ከፍ አልሽን? ወደ ሲኦል ትወርጃለሽ፤ በአንቺ የተደረገው ተአምራት በሰዶም ተደርጎ ቢሆን፥ **እስከ** ዛሬ በኖረች ነበርና*።» ***ማቴ 11፡23***፣

# የእመቤታችን ዘላለማዊ ድንግልና

***‹‹እስከ›› የሚለው ቃል ትርጉም***

- «እነሆም እኔ <u>እስከ</u> ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።» ***<u>ማቴ 28፡20</u>***፣ «ፍጥረት ሁሉ <u>እስከ</u> አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና።» ***<u>ሮሜ 8፡22</u>***፣ «<u>እስክመጣ</u> ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ።» ***<u>ቀዳ ጢሞ 4፡13፡፡</u>***
- የማቴ 1፡25 ትርጉምም «ከመወለዱ በፊት አረጋዊው ዮሴፍ እመቤታችንን ከመጠበቅ በቀር በግብር አይተዋወቁም፣ ጌታ እግዚአብሔር ወልድ በዘር በሩካቤ አልተጸነሰም፤ ነገር ግን በመንፈስቅዱስ ተጸንሶ ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ተወለደ።» ማለት ነው፡፡
- «እስከ» የሚለው ቃል የሚያስረዳን «ከመወለደ በፊትን» ሲሆን ከዚህ በቀር ቅዱስ መጽሐፍ ከዚያ በኋላ ስለ እመቤታችን በግብር መተዋወቅ ያነሳበት ክፍል የለም፡፡ እኛም ያልተጻፈልንን አንተረጉምም፣ አናምንማ አናሳምንም፡፡ ይልቁኑ ከልጅዎ ሳትለይ በኅቱም ድንግልና ኖረች እንላለን እንጂ፡፡ ***<u>ሕዝ 44፡1-2፡፡</u>***

***‹‹በኩር›› የሚለው ቃል ትርጉም***

- በግሪኩ በኩር የሚለው *"prototokos"* ቃል ለበኩር ተከታይ እንዳለው አድርጎ አልተቀመጠም ወይም አልተገለጠም፡፡
- ***<u>በዕብ 1፡6</u>*** ‹‹ከመላእክትስ፡፡ አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ፥ ደግሞም፦ እኔ አባት እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል ያለው ከቶ ለማን ነው? ደግሞም ***<u>በኵርን</u>*** ወደ ዓለም ሲያገባ፡፡ የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ ይስገዱ ይላል።» ተብሎ የተጠቀሰው «በኩር» የአምላክን (የቃልን) ሰው መሆንን ከመጥቀስ ባለፈ «ሁለተኛ ልጅ» እንዳለ አመልካች ኤአደለም፡፡
- «በኩር» የሚለው ቃል በቅዱስ መጽሐፍ በየትኛውም ክፍል ውስጥ ለሁለተኛ ወይም ለሦስተኛ ልጅ መኖር ማረጋገጫ የሚሰጥ ትርጉም ይዞ አልተጻፈልንም፡፡
- ይልቁኑ « ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል <u>በኵር</u> ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና።» ***<u>ሮሜ 8፡29</u>***፣ « በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው፡፡ ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፡፡ እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፡፡ እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ፥ መጀመሪያ ከሙታንም <u>በኵር</u> ነው።» ***<u>ቆላ 1፡15 እና 18</u>*** « አጥፊው <u>የበኵሮችን</u> ልጆች እንዳይነካ ፋሲካንና ደምን መርጨትን በእምነት አደረገ።» ***<u>ዕብ 11፡28</u>*** « በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር፥ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፥ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፥» ***<u>ዕብ 12፡23</u>***፣ « ከታመነውም ምስክር ከሙታንም በኵር» ***<u>ራእ 1፡5</u>*** በማለት ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአባቱ አንድያ ልጁ እንደሆነ እንረዳና ለእግዚአብሔር አብ ሁለተና የባህርይ ልጅ አለው ብለን ከማሰብ እንቆጠብ ዘንድ ተጽፎልናል እንጂ ስለእናቱማ ጽፎልን ቢሆን በሌሎቹ ክፍሎች በግልጥ እንዳደረገው ስምዋን ጠቅሶ መናገር ምን አዳግቶት?!

# <u>እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም</u>

- ቅዱስ ገብርኤል «ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ» እንዳላት እመቤታችን በመንፈስቅዱስ ኃይል ጌታችንን ጸንሳ ወልዳለች፡፡ የጌታችን እናቱ እመቤታችን በሄደበት ሳትለየው በትሕትና ኖራለች፡፡
- እመቤታችን የሰማይና የፍጥረት ሁሉ ንግሥት ናት፡፡ ልበ አምላክ ዳዊት በመዝሙሩ « በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች:: ልጄ ሆይ፥ ስሚ እዪ ጆሮሽንም አዘንብዪ ወገንሽን ያባትሽንም ቤት እርሺ ንጉሥ ውበትሽን ወድዶአልና፥ እርሱ ጌታሽ ነውና፡፡... ለልጅ ልጅ ሁሉ ስምሽን ያሳስባሉ፡፡» በማለት ***<u>በመዝ 44</u>*** ላይ የዘመረላት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት፡፡
- ቅድስናዋም ለማንም ባልተደረገው በአምላክ እናትነትዋ... ***<u>ሉቃ 1፡43፡፡</u>*** ነውና ከቅዱሳንና ከመላእክት ቅድስናም ስለሚልቅ ቅድስተ ቅዱሳን እንላታለን፡፡
- የአምላክ እናት በመሆንዋ በመስቀሉ ሥር በቅዱስ ዮሐንስ በኩል እናት ሆና እንደተሰጠችን በአምላካችን ፊት ስለ እኛ ስለልጆችዋ ትለምንልናለች ታማልደናለች እንጂ ሥራ እንደማይሠሩበት ሥልጣን በከንቱ በአምላክ እናትነትዋ ቸል አትለንም፡፡ መናገር ማሰብ፣ መስማት ... ለሚችሉ ነገር ግን ለተጎዱ ወገኖች የሚናገሩላቸው (Advocates) አሉ... ለእኛም በንጉሡ በእግዚአብሔር ፊት የምትነግርልን፣ የምታስረዳልን፣ የምታማልደን እርስዋ እመቤታችን ናት፡፡
- ***<u>በራእይ 12፡1</u>*** እንደተገለጸው ፀሐይን የተጎናፀፈችው እርስዋ ናት፡፡ እመቤታችን በቅዱስ መጽሐፋችን አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፣ የእግዚአብሔር ከተማ፣ የጽዮን ተራራ፣ ... ተብላ እየተመሰለች ተጠቅሳለች፡፡
- ለእመቤታችን ያለን ይህ ፍቅር የመነጨውም የሚመራንም ወደ ጌታችን ወደ አምላካችን ወደ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ የእመቤታችን መልእክትዋ «ልጄ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» የሚል ነውና፡፡
- በቃናው የሠርግ ቤት የእመቤታችን አማላጅነት የጠቀማቸው ሠርገኞች ለርስዋ ያላቸው ፍቅር ቃልዋን ሰምተው እንዲፈጽሙ አደረጋቸው እንጂ በቅዱስ መጽሐፍ ከተጻፈው መንገድ አላወጣቸውም ወይም ፈቀቅ እንዲሉ አላደረጋቸውም፡፡
- እኛም እንደ ቃናው የሠርግ ቤት ሠርገኞች የእመቤታችን አማላጅነትና የፍቅር ቃልዋን ሰምተን ልጅዋ አምላካችን የሚለንን እንድንፈጽም ያደርገናል እንጂ በቅዱስ መጽሐፍ ከተጻፈው መንገድ አያወጣንም አላወጣንምም፡፡ ስለዚህ በአማላጅነትዋና በፍቅሯ ተጠቅመን የአምላካችንን ፈቃድ ለመፈጸም ያብቃን፡፡

# ይቆየን...

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org